# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡-

# የወቅቱ ችግሮች፣ተግዳሮቶች እና ፈተናዎች

ለሰሜን አሜሪካ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ጉባኤ የቀረበ

ዴንቨር፣ ነሐሴ 27 ቀን 2003 ዓም

## ጠቅላላ መግቢያ

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ታሪክ ገጽታዎች

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ታሪክ የሚባለው የራስዋ ሲኖዶስ ኖሯት ራስዋን መምራት ከጀመረችበት በኋላ ያለው ታሪክ ነው። ይህንን የታሪክ ምእራፍ ከቀደምቱ ልዩ የሚያደርጉት ገጽታች አሉ።

1. የቤተ ክርስቲያኒቱ ሁለት ገጽታዎች በሚገባ ተለይተው የታወቁበት ዘመን መሆኑ።

እነዚህ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሁለት ገጽታዎች የምንላቸው

ቤተ ክርስቲያናዊ ገጽታዋን እና ቤተ ክህነታዊ ገጽታዋን ነው።

## ቤተ ክርስቲያናዊ ገጽታ

ቤተ ክርስቲያናዊ ገጽታ የምንለው ትምህርተ ሃይማቷን፣ ሥርዓትዋን፣ ትውፊቷን፣ ቅዳሴዋን፣ መጻሕፍቷን ወዘተ ነው። ይህ ገጽታዋ ሃይማኖታዊውን ጉዞዋን ብቻ ያሳያል።

### ቤተ ክህነታዊ ገጽታ

ቤተ ክህነታዊ ገጽታዋ የቤተ ክርስቲያኒቱን የሰው ኃይል፣ የንብረት፣ የገንዘብ፣ የቦታ፣ የሕግ፣የአሠራር ወዘተ ገጽታዋ ነው። በዚህ ዓለም ላይ እንደ መኖርዋ መጠን እንደ ማንኛውም መሥሪያ ቤት የሚኖሯት መዋቅሮች፣ አሠራሮች፣ ደንቦች፣ የሰው ኃይል እና የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ አውታሮች አሉ።

የመጀመርያው ለሁለተኛው መሠረት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ለመጀመርያው ድጋፍ ሰጭ ነው። የመጀመርያው መሥመሩን ከሳተ ቤተ ክርስቲያኒቱ በጠቅላላው መሥመ ሯን ትስታለች። ሁለተኛው መሥመሩን ከሳተ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሚገባ ተልዕኮዋን እንዳትወጣ ትገደባለች።

2 መንግሥት እና ሃይማኖት በሕግ የተለያዩበት ዘመን መሆኑ

ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱ የትምህርት፣ የሥልጣኔ፣ የሞራል፣ የሕግ፣ የሥልጣን ምንጭ ሆና ለዘመናት ኖራለች። ነገሥታን ቀብታ ታነግሥ የነበረች፤ አስፈላጊ ሲሆንም ሥልጣናቸውን ነጥቃ ታሰናብት የነበረች ተቋምም ነበረች።

ከ1966 ዓም በኋላ የተከሰተው እና መንግሥት እና ሃይማኖትን የለያየው ፍልስፍና በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ እንግዳ ክስተት ነው:: ምክንያቱም በሕግ መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን ቢለያዩም የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥልጣን እና ዐቅም ተዳከመ እንጂ በአሠራር ግን መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን የተለያዩበትን ሁኔታ ለማየት አስቸጋሪ የሚሆንባቸው ነገሮች አሉና::

## 3 የቤተ ክርስቲያኒቱ የኢኮኖሚ ሥሪት መቀየር

ለ2000 ዘመናት ያህል የቤተ ክርስቲያኒቱ የኢኮኖሚ ሥሪት መሬትን መሠረት ያደረገ ነበር:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያኒቱ የኢኮኖሚ ድህነት ጥያቄ አልነበረባትም:: የ1966 ዓም አብዮት ያለ ዝግጅት በድንገት የቤተ ክርስቲያኒቱን የኢኮኖሚ መሠረት ከመሬት ወደ ምእመናን መዋጮ ቀየረው:: ይህ ሁኔታ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ ኢኮኖሚ ድህነት፣ ካህናቱንም ወደ ጥገኛነት ቀየራቸው::

## 4 ሁለት ዓይነት የተማሩ ትውልዶች መከሰት

ቀድሞ በሀገሪቱ ይፈጠሩ የነበሩ ምሁራን በቤተ ክርስቲያኒቱ የትምህርት ሥርዓት የሚያልፉ ነበሩ:: የሀገሪቱን መንግሥታዊም ይሁን መንግሥታዊ ያልሆነውን ሥልጣን የሚይዙት እነዚሁ ከቤተ ክርስቲያኒቱ የትምህርት ተቋማት የሚወጡት ምሁራን በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ በሀገሪቱ የሥልጣን፣የአስተሳሰብ፣ የእምነት፣ የሞራል እና የሥርዓት ሁኔታዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የማሳረፍ ዐቅም ነበራት::

በዘመናዊው የሀገሪቱ ታሪክ የተፈጠሩት ዘመናውያን ትምህርት ቤቶች ግን የተማረውን የሀገሪቱን ትውልድ ወደ ሁለት ከፈሉት:: በአንድ በኩል ከነባር የቤተ ክርስቲያኒቱ ትምህርት ቤቶች የሚወጣ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የሚወጣ:: ከነባር ት/ቤቶች የሚወጣው ዘመናዊውን ሳያይ መምጣቱ፣ በዘመናዊው የትምህርት ተቋማት የሚያልፈውም ነባሩን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሳያይ ማደጉ ሁለቱም መንታ ሆነው እንዲወጡ አደረጋቸው::

ይህ ሁኔታ ደግሞ ተጣጥመው መጓዝ የነበረባቸውን የሀገሪቱን ትውልዶች እርስ በርስ የሚተጋገሉ እንዲሆኑ አድርጓል:: በተላይም በሀገሪቱ የሥልጣን፣ የሕግ፣ የቢሮክራሲ፣ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የባህል፣ የትምህርት እና የሚዲያ ተቋማት ውስጥ በብዛት የሚገባው ትውልድ ከዘመናዊው የትምህርት ተቋማት የሚወጣው ትውልድ መሆኑ የቤተ ክርስቲያኒቱን የተጽዕኖ ክልል አጥብቦታል::

## 5 የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት በዓለም ዐቀፍ ደረጃ መስፋፋት

ቤተ ክርስቲያን በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እና በግብጽ ከነበሯት አብያተ ክርስቲያናት በተጨማሪ በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች አዳዲስ አጥቢያዎች የተተከሉት በዘመናዊው የቤተ ክርስቲያኒቱ የታሪክ ዘመን ውስጥ ነው።

በአውሮፓ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአሜሪካ እና በአውስትራሊያ ብሎም በመካከ ለኛው የአሜሪካ ሀገሮች አያሌ አጥቢያዎችን ተክላለች። ነገር ግን ለእነዚህ የሚመጣጠን የሰው ኃይል፣ የአሠራር ሥርዓት፣ ሕግ፣ የመገናኛ እና የመረጃ አውታር አለዘረጋችም።

እነዚህ ቤተ ክርስቲያኒቱ የገጠሟት አዳዲስ ክስተቶች ወደ ኋላ ላይ ላጋጠሟት ችግሮች፣ ፈተናዎች እና ተግዳሮቶች ከፍተኛውን አስተዋጽዖ አድርገዋል።

## የቤተ ክርስቲያን ችግሮች፣ ፈተናዎች እና ተግዳሮቶች

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ላይ የምትቀዝፍ ሰማያዊት መርከብ በመሆንዋ ዓለም አትስ ማማትም። ይህንን ሰማያዊ ጉዞዋን ስታከናውን በመንገዷ ላይ ሦስት ነገሮች ይገጥ ሚታል። ችግሮች፣ ፈተናዎች እና ተግዳሮቶች። በዝርዝር እናያቸዋለን።

## ችግሮች

ችግሮች የሚባሉት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚከሰቱ የአሠራር፣ የአወቃቀር እና የአመለካከት ውስንነቶች ናቸው:: እነዚህ ችግሮች ቤተ ክርስቲያኒቱ ከፋይናንስ እጥ ረት፣ ከተማረ የሰው ኃይል እጥረት፣ ከቁሳቁስ እጥረት፣ ከዕውቀት እጥረት እና ከሥ ርዓት እጥረት ሊከሰቱባት ይችላሉ:: ለምሳሌ ደረጃውን የጠበቀ መዋቅር አለመኖር፣ በቂ እና የተማረ የሰው ኃይል አለመኖር፣ የፋይናንስ ሥርዓቱ የተሳለጠ አለመሆን፣ የት ምህርት ተቋማቷ በሚገባ አለመደራጀት፣ የመረጃ እና የመገናኛ ሥርዓት አለመኖር በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚፈጥሯቸውን እንከኖች ችግሮች እንላቸዋለን::

እነዚህ ችግሮች ከውስጥ ዋነኛ መገለጫቸው የሚመነጩት ከውስጥ የአሠራር እና የአመለካከት ድክመት መሆኑ ነው:: በሌላም በኩል ደግሞ የእነርሱን የተጽዕኖ ዐቅም መቀነስ እንጂ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ማጥፋት አይቻልም:: በዘመነ ሐዋርያት በኢየ ሩሳሌም የነበሩ ምእመናንን በመመገብ ረገድ የተነሣው የአስተዳደር ጥያቄ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው:: በነዚያ በበቁት ሐዋርያት ዘመን የተነሣው የአስተዳደር ጥያቄ ዛሬም በተለያየ ገጽታ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ይነሣል::

የቤተ ክርስቲያን ችግሮች ተጽዕኖአቸው እየሰፋ ከሄደ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዐቅም ስለሚያዳክሙ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለሌሎች ፈተናዎች የተጋለጠች ያደርጓታል:: አንዲት ቤተ ክርስቲያን ከፈተናዎች ውጭ ሆና መኖር አትችልም:: የምትችላው ፈተናዎችን መቋቋም እና ማሸነፍ ብቻ ነው:: እነዚህን ፈተናዎች ለመቋቋም እና ለማሸነፍ ደግሞ ከምንም በላይ ውስጣዊ መንፈሳዊ እና መዋቅራዊ ጥንካሬ ወሳኞች ናቸው::

የቤተ ክርስቲያን ችግሮች እየተባባሱ ሲመጡ ግን መንፈሳዊም ሆነ መዋቅራዊ ዐቅሟ ይዳከምና አጠር እንደሌለው የወይን እርሻ የየትኛውም ፈተና መራኮቻ ትሆናለች:: አሁን የምናየውም ይህንኑ ነው::

## ተግዳሮቶች

ተግዳሮቶች የምንላቸው ቤተ ክርስቲያን ከሚኖረው የዓለም ሥርዓት የሚመጣባትን ግፊት ነው:: የዓለም ሥርዓት በየጊዜው ይቀያየራል:: ይህ የዓለም ሥርዓት መቀያየር

ደግሞ የተለያዩ አመለካከቶችን፣ የአሠራር መንገዶችን፣ ጥያቄዎችን፣ ማኅበራዊ ክዋኔ ዎችን፣ የፖለቲካ ሂደቶችን እና የግንኙነት መንገዶችን ይፈጥራል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ እንደ መኖርዋ፣ የምታገለግላቸው ልጆቿም በዚህ ዓለም ላይ እነደ መኖራቸው መጠን ከዚህ የዓለም ጉዞ ተግዳሮቶች ይገጥሚታል፡፡ የዴሞክራሲ እና የሰብአዊ መብት መሠረተ ሃሳቦች፣ በጋብቻ ላይ የተፈጠሩ አዳዲስ አመለካከቶች፣ የሉላዊነት ወይንም ግሎባላይዜሽን ሂደት፣ የኢንተርኔት፣ የሚዲያ እና ፊልም መስ ፋፋት፣ ስለ እምነት የሚነሡ አዳዲስ ሃሳቦች እና ጥያቄዎች፣ የአንድ ሀገር የፖለ ቲካ እና የዕውቀት ኃይሎች የሚያደርጉባት ግፊት፣ አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶች፣ ወዘተ የቤረ ክርስቲያኒቱ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ተግዳሮቶች ማስቀረትም ሆነ መቀነስ አትችልም፡፡ ምክንያቱም የሚሙት ከእርስዋ ውጭ ካሉ አካላት ነውና፡፡ መቋቋም እና ማሸነፍ ግን ትችላለች፡፡ የእነዚህ ተግዳሮቶች መኖር ቤተ ክርስቲያንን ሊጠቅማትም ሆነ ሊጎዳት ይችላል፡፡ ቤተ ክርስቲያን አሠራርዋን እንድትፈትሽ፣ እንድትዘጋጅ እና እንድትተጋ በማድረግ ረገድ ተግዳሮቶች ጥቅም አላቸው፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ከላይ ያነሳናቸው የቤተ ክርስቲያን ችግሮች ቤተ ክርስቲያኒቱን እጅ ከወርች አሥረው ካልያዟት ነው፡፡ የእነዚህ ተግዳ ሮቶች መኖር ቤተ ክርሰቲያኒቱ ትምህርቷን እና ሥርዓትዋን በሚገባ እንድታብራራ፣ እንድታስረዳ እና እንድትጽፍ ያደርጓታል፡፡ አዳዲስ የመገናኛ አውታችን እንድትጠቀም ያስገድዷታል፡፡ የሰው ኃይል ሥልጠናዋን እንድታሳድግ ያደርጓታል፡፡ የስብከት ዘዴዋን እና መንገዷን እንድታበለጽግ ያስችሏታል፡፡ የትምህርት ተቋማቷን በትምህርት ጥንታ ውያን በአሠራር ዘመናውያን እንዲሆኑ ያደርጓታል፡፡ መዋቅሯን እና የአሠራር ሥርዓ ትዋን በየጊዜው ለማሳደግ ያስችሏታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቱ በውስጣዊ ችግሮች ከተያዘች እነዚህ ከዓለም የሚመጡ ተግዳሮቶች ያለ ምንም ተቋቋሚ ሰተት ብለው ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲ ዘልቁ ያስችላቸዋል፡፡ ይኼ ሲሆን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ማሸነፍዋ ይቀርና ዓለም ቤተ ክርስቲያኒቱን ታሸንፋታለች፡፡ ዛሬ በፕሮቴስታንቱ ዓለም የምናየው የዓለምን አመለካከት፣አሠራር፣ ቴክኖሎጂ፣ ፍልስፍና እና የኑሮ ሥርዓት ሁሉ እንዳለ የመቀበል ሂደት የተከሰተው አብያተ ክርስቲያናቱ በውስጣዊ ችግሮች ተበልተው በማለቃቸው እና ለውጫዊ ተግዳሮቶች በራቸውን ወለል አድርገው በመክፈታቸው ነው፡፡

ዓለም ለሚያመጣቸው ተግዳሮቶች ቤተ ክርስቲያን ምንጊዜም ሦስት ዓይነት መልሶች ይኖሯታል፡፡

- *የምትቀበላቸው*
- *የምታሻሽላቸው እና*
- *የምትቃወማቸው።*

ከተልዕኮዋ፣ ከትምህርቷ እና ከዓላማዋ ጋር የሚሄዱትን፤ ጌታዋ መድኃኒቷ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጣትን አደራ እነ ተልዕኮ ለመወጣት ይበልጥ የሚያስችሏትን፣ ምንም ዓይ ነት የእምነት እና የሥርዓት መፋለስ የማያመጡትን ተግዳሮቶች ትቀበላቸዋለች። መጠ ነኛ ለውጥ ተደርጎባቸው ከእምነቷ እና ሥርዓቷ ጋር ሊሄዱ የሚችሉትን አሻሽላ እና ሞርዳ ትቀበላቸዋለች። ፈጽመው ከተልዕኮዋ፣ እምነት እና ሥርዓትዋ ጋር የማይሄዱትን ደግሞ ትቃወማቸዋለች።

አንዲት ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ነገሮች እንደየአስፈላጊነቱ የማታደርግ ከሆነ ጉዞዋን አስቸጋሪ ያደርጉባታል። ማንኛውንም ዓይነት ተግዳሮቶች የማትቀበል እና የምትቋቋም ከሆነ ከትውልዱ እየራቀች ትሄዳለች። ሁሉንም ዓይነት ተግዳሮቶች የምትቀበል ከሆነ ደግሞ ትውልዱን መምራት ትታ በትውልዱ መመራት ትጀምራለች። በቤተ ክርስ ቲያን እና በዓለም መካከል ያለው መሥመርም ፈጽሞ ይጠፋል።

## ፈተናዎች

ፈተናዎች የሚባሉት በትምህርተ ሃይማኖቷ፣ በሥርዓትዋ እና በትውፊቷ ላይ የሚቃጡ ዘመቻዎች ናቸው። እነዚህ በዋነኛነት ከመናፍቃን፣ ከከሃድያን፣ ከጣዖት አምላኪዎች፣ በአጠቃላይም ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ዘመቻዎች ናቸው። የእነዚህ ዘመ ቻዎች ዓላማ ቤተ ክርስቲያኒቱን ቀይሮ ሌላ ተልዕኮ መስጠት ነው። እነዚህ ኃይሎች ቤተ ክርስቲያኒቱ አጥፍተው ሌላ ተቋም እስካልተኩ ድረስ የማይረኩ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ጉዞ ውስጥ አስቸጋሪው እና ከባዱ ነገርም ይኼው ነው።

# አሁን ቤተ ክርስቲያን ያጋጠሟት ችግሮች ፈተናዎች እና ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

## ችግሮች

ቀደም ብለን የቤተ ክርስቲያንን ሁለት ዓይነት ገጽታዎች ተመልክተናል።

ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ችግርዋ «ቤተ ክህነታዊ» ገጽታዋ ነው። ይህ ገጽታዋ ቤተ ክርስቲያኒቱ በየዘመናቱ ከሚፈጠረው ትውልድ እና አሠራር ጋር እንድትራመድ፣ ሲሆንም ለትውልድ የሚተርፍ የተሻለ አሠራር እንድትዘረጋ የሚያደርጋት ነው።

ቤተ ክርስቲያናዊው ገጽታዋ ከሰማዕትነት፣ ከድካም፣ ከአትኅቶ ርእስ፣ ከመንኖ ጥሪት ጋር የሚሄድ ሲሆን ቤተ ክህነታዊ ገጽታዋ ግን ከክብር፣ ከጥቅም እና ዝና ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከቤተ ክርስቲያናዊ ገጽታዋ ይልቅ ለአደጋ የተጋለጠ አድርጎታል።

በተለይም ቤተ ክርስቲያኒቱ በእምነት እና በሥርዓት ብሎም በመንፈሳዊ የሥልጣን ተዋረድ ecclesiastical order ትመራበት ከነበረው ከ1950 በፊት ከነበረው ዘመን ይልቅ በቢሮክራሲያዊ የሥልጣን ተዋረድ ወደ መመራት ከመጣችበት ከ1950 በኋላ ባለው ዘመን አስተዳደር ነክ፣ ገንዘብ ነክ እና ሥልጣን ነክ የሆኑ ችግሮች እየተባባሱባት መጥተዋል።

የዚህ ዋናው ምክንያት እንደ ትምህርተ ሃይማኖቷ፣ ሥርዓቷ እና ትውፊቷ ሁሉ የነጠረ፣ የጠራ እና የቀና ነገር ስለሌለ ነው። ዛሬ ዛሬ ምእመናኗ በራሳቸው ፍላጎት ለአገልግሎት በተነሡበት ዘመን፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ለመሳተፍ በራሳቸው የመጡ አያሌ ማኅበራት በተደራጁበት ዘመን፣ ከአንድ ጳጳስ አልፋ ስድሳ እና ሰባ ጳጳሳት ባሏት ዘመን፣ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችን ባደራጀችበት ዘመን ከበፊቱ በባሰ በአስተዳደር፣ በገንዘብ እና በአሠራር ላይ ከምእመናንም ሆኑ ከካህናት የሚቀርቡ ቅሬታዎች እየባሱ ለምን መጡ?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የቤተ ክህነቱን መሠረታዊ ችግሮች መመልከት ይገባል። ብዙ ሰዎች እንደ ሚመስላቸው የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን አደጋዎች ቤተ ክርስቲያንን እናድሳለን የሚሉ አካላት መነሣት፤ የገዳማት እና አድባራት መቸገር፤ በስብከተ ወንጌል መድረኮች ዙርያ እየታዩ የመጡ ክስተቶች፣ ያሬዳዊ ያልሆኑ መዝሙራት መብዛት፣ «የባሕታውያን» ማደናገር፣ ወዘተ አይደሉም። እነዚህ ነገሮች መኖራቸው ርግጥ ነው። ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያኒቱ አደጋ እስከመሆን የደረሱት ሥር የሰደዱ የውስጥ ችግሮች በመኖራቸውና የመቋቋም ዐቅማችን በመዳከሙ ነው።

ዋናዎቹ የቤተ ክህነቱ ችግሮች ሲፈቱ ከላይ የጠቀስናቸውና ሌሎቹም ችግሮች አብረው ይፈታሉ።

እስካሁን ልዩ ልዩ አገልጋዮች፣ ማኅበራት እና ኮሚቴዎች ተነሥተው ከላይ የጠቀስናቸውን ችግሮች ለመፈታት ታግለዋል። ነገር ግን የሚራቡ ገዳማት፣ ደመወዝ የሚያጡ ካህናት፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የሚነሡ ተቃዋሚዎች፣ ሳይቀደስባቸው የሚውሉ አጥቢያዎች፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት ውጭ የሚሰበኩ ስብከቶች እና የሚዘመሩ መዝሙሮች ቁጥራቸው እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ ሊመጣ አልቻለም።

ይህ ሁኔታ አንድ ነገር ይጠቁመናል። የችግሮቹን የስበት ማዕከል አለማግኘታችንን። የችግሮች የስበት ማዕከል ማለት ለሌሎች ቅርንጫፍ ችግሮች መራባት ምክንያት የሆነ እና እርሱ ሲፈታ ቅርንጫፍ

ችግሮቹም አብረው ሊፈቱ የሚችሉ ችግር ማለት ነው፡፡ የስበት ማዕከሉን ትቶ ቅርንጫፍ ችግሮችን ብቻ እየፈቱ መጓዝ ሁለት አይነት መከራ ያመጣል፡፡

የመጀመርያው ኃላፊነት የተሰጠው አካል እርሱ ምንም አስተዋጽዖ ሳያደርግ ሥራው ስለ ሚሠራለት ትኩረቱን ወደ ግል ጥቅሙ እና ዝናው እንዲያደርግ ያስችሉታል፡፡ ችግር ለመፍታት የተነሣው አካል ሁለተኛው ደግሞ ችግሮቹን ከመሠረታቸው ከመፍታት ይልቅ እንጥፍጣፊዎች ላይ ስለሚያተኩር ችግሮቹ ዘላቂ ችግሮች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

በመሆኑም ቤተ ክርስቲያንን በአንድም በሌላም መልኩ እናገለግላለን፣ አስተዋጽዖ እናደርጋለን፣ ገንዘባችንን፣ ጊዜያችንን እና ዕውቀታችንን እንሠዋለን ብለው የተሰባሰቡ አካላት እና ግለሰቦች የማርሽ ለውጥ ማድረግ ያለባቸው ጊዜ አሁን ይመስለኛል፡፡ ከቅርንጫፍ ችግሮች ወደ ችግሮቹ የስበት ማዕከል መዞር፡፡

ለመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክህነቱ የችግር የስበት ማዕከል ምንድን ነው?

በአሁኑ ጊዜ ያለው የቤተ ክህነቱ የችግር የስበት ማዕከል ሲኖዶሱ ነው፡፡ ሲኖዶሱ ቢስተካከል እና በበቂ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያኒቱን ቢመራት ኖሮ አሁን የምናያቸው ችግሮች አይፈጠሩም፤ ቢፈጠሩም በጊዜ ይታረሙ ነበር፡፡

ለምንድን ነው የችግሮቹ የስበት ማዕከል ሲኖዶሱ ነው የተባለው?

የቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረሻ ወሳኝ አካል ሲኖዶሱ ነው፡፡ ሕግ ማውጣት፣ ቀኖና መደንገግ፣ አሠራር መዘርጋት፣ ችግሮችን ለመጨረሻ ጊዜ መፍታት፣ ስሕተቶችን ማረም እና እንቅፋቶችን ማስወገድ የሚችለው እርሱ ነው፡፡ መንፈሳዊም ምድራዊም ሥልጣን አለውና፡፡ መንፈሳዊው ሥልጣን በመንፈስ ቅዱስ እና በቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጠ፤ ምድራዊ ሥልጣን በሀገሪቱ ሕግ የተደነገገ ነው፡፡

ነገር ግን ሲኖዶሱ ራሱ በችግሮች ተተብትቦ ተይዟል፡፡ ዐቅም አግኝቶ ውሳኔ መወሰን አልቻለም፤ ቢወስንም አያስፈጽምም፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብ እና ንብረት ላይ በሙሉ ሥልጣኑ አያዝም፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን እርከኖች ላይ በሙሉ ሥልጣን አያዝም፡፡ የመቆጣጠርያ፣ የመከታተያ እና የማስፈ ጸሚያ ስልትና አሠራር የለውም፡፡

የቤተ ክህነቱን አሠራር፣ ሕግጋት፣ ሥርዓት እና አስተሳሰብ አሁን ቤተ ክርስቲያን እና ሀገሪቱ በምት ፈልገው መጠን ማስተካከል እና ደረጃውን ከፍ ማድረግ አልቻለም፡፡ ይህንን እንዳያደርግ ደግሞ እርሱ ራሱ በመሠረታዊ ችግሮች ተይዟል፡፡

ይህን የችግር የስበት ማዕከል ቀፍድደው የያዙት አራት መሠረታውያን ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ስንፈታ የስበት ማዕከሉ ችግር ይፈታል፤ የስበት ማዕከሉ ችግር ሲፈታ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር ይፈታል፡፡

አራቱ መሠረታውያን ችግሮች የምንላቸው የመንፈሳዊነት መዳደል፣ ሙስና፣ መንደርተኛነት እና ኋላ ቀርነት ናቸው፡፡

## 1 የመንፈሳዊነት መዳደል

መንፈሳነት የመጀመርያው እና የመጨረሻው ወሳኙ ነገር ነው፡፡ መንፈሳውያን በሌሉበት ቦታ መንፈሳዊ ነገር መፍትሔ አያገኝም፡፡ መንፈሳዊነት ማለት የሃይማኖትን ትምህርት ማወቅ፤ ቤተ ክርስቲያን መሄድ፤ የቃል ጸሎትን መሸምደድ፣ የቤተ ክርስቲያንን መዓርጋት መያዝ፤ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ማገልገል ማለት ብቻ አይደለም፡፡ እነዚህ መንፈሳዊነትን የሚያጎለብቱ ነገሮች እንጂ በራሳቸው መንፈሳዊነት አይደሉም፡፡

መንፈሳዊነት ኑሮ ነው፤ አመለካከት ነው፤ ሕይወት ነው፤ ቅኝት ነው፡፡ መንፈሳዊነት በፈሪሃ እግዚአብሔር ተቃኝቶ፤ በቃለ እግዚአብሔር ተመርቶ፤ መንፈሳዊን ጥበብ ገንዘብ አድርጎ ውስጥን መለወጥ ነው፡፡

አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በምንም መንገድ ካልፈራ፤ ቃለ እግዚአብሔርን ከተለማመደው፤ የማያ ምንባቸውን ነገሮች ለሥነ ሥርዓት ሲል ብቻ የሚያደርግ ከሆነ፤ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ነገር ከስሕተቱ ካላቆመው፤ «እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር» ከሚባልበት ደረጃ ደርሷል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሰው የተአምራት ቅጣት እንጂ ምክር እና ተግሣጽ አይመልሰውም፡፡

በመሆኑም የሳኦልን ኃጢአት የሚመክት የዳዊት መንፈሳዊነት፤ የኤልዛቤልን ኃጢአት የሚመክት የኤልያስ መንፈሳዊነት፤ የድርጣድስን ኃጢአት የሚመክት የጎርጎርዮስ መንፈሳዊነት፤ የብርክልያን ኃጢአት የሚመክት የዮሐንስ አፈወርቅ መንፈሳዊነት፤ የግራዚያኒን ኃጢአት የሚመክት የአቡነ ጴጥሮስ መንፈሳዊነት፤ በቤተ ክህነታችን ጎድሏል፡፡

ዛሬ ዛሬ መንፈሳዊ አገልግሎት አገልግሎት መሆኑ ቀርቶ የቢሮ ሥራ ሆኗል፡፡ መቀደስ፣ ሰዓታት መቆም፣ ፍትሐት መፍታት፣ ኪዳን ማድረስ፣ ማኅሌት መቆም ሥራ ብቻ ነው፡፡ የጽደቅ አገልግሎት መሆኑ እየተረሳ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በዓለማዊ መሥሪያ ቤቶች እንኳን የማናየውን የጉቦ፣የዘመድ አሠራር፣ የፍትሕ መዛባት፣ አምባገ ነንነት፣ ሥርቆት እና ሌሎች ነገሮችን በእኛ ዘንድ መስማት ነውርነቱ አልፎበታል፡፡

መዋቅር እና አሠራርን የሚያጠኑ ሰዎች እንደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚያመሰግኑት የለም፡፡ ብዙዎቻችን ልምድ ልንቀስምባቸው የሚያስችሉ አሠራች እና አወቃቀሮች አሏቸው፡፡ ነገር ግን ዋናው ነገር መንፈሳዊነቱ ጎደለና ዛሬ ዛሬ የካቶሊክ ካህናት የሚወቀሱት ሕፃናትን በመዳፈር ሆነ፡፡ «ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡታል፣ ውኃ ቢያንቅ በምን ይውጡታል» የተባለው ደረሰ ማለት ነው፡፡

አንድ የጥንት አባት «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቁ ችግር የሚፈጠረው መንፈሳውያን ያልሆኑ ሰዎች መንፈሳዊ ሥራ ሲሠሩ ነው» ብሎ ነበር፡፡ ያልመነኑ ሰዎች ከመነኮሱ፤ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ከቀሰሱ፤ እግዚአብሔርን የማያውቁት ሰዎች ካስተማሩ፤ ደመወዝ፣ቤት እና መኪና የሚያጓጓቸው ሰዎች ከጳጳሱ፤ ፍትፍት ያልሰለቻቸው ሰዎች ባሕታውያን ከሆኑ፤ የዘር ዛር ያልለቀቃቸው ሰዎች የሁሉ አባት ከተባሉ፤ ከራሳቸው ጋር ያልታረቁ ሰዎች ለታራቂነት እና አስታራቂነት ከተቀመጡ፤ መንፈሳዊነት ሽታውም ጠፍቷል ማለት ነው፡፡

ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ለመንፈሳዊ ችግሮች የታክቲክ እና የቴክኒክ እንጂ የመንፈስ መፍትሔ ስንፈልግ የማንገኘው፡፡

አንዳንድ ጊዜኮ እኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለን፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ከእኛ ውስጥ ወጥታለች፤ እኛ በክርስትና ውስጥ ነን፤ ክርስትና ግን ከእኛ ውስጥ ወጥቷል፤እኛ በክህነቱ ልብስ ውስጥ ነን፤ ክህነቱ ግን ከእኛ ውስጥ ወጥቷል፤ እኛ በስብከቱ ቀሚስ ውስጥ ነን፤ ስብከቱ ግን ከውስጣችን ወጥቷል፡፡ እኛ በገዳም እንኖራለን፤ ገዳማዊ ሕይወት ግን በኛ ውስጥ የለም፡፡ ለአንዳንዶቻችን ጵጵስና ፕሮፌሽን ነው፤ ቅስና ፕሮፌሽን ነው፣ ሰባኪነት ፕሮፌሽን ነው፤ ምንኩስና ፕሮፌሽን ነው፤ ዝማሬ ፕሮፌሽን ነው፣ እንደ ጥብቅና፣ እንደ ንግድ፣ እንደ ሕክምና፣ እንደ ጋዜጠኛነት፣ እንደ ምሕንድስና፣ የእንጀራ ማግኛ ሞያ፡፡ ታድያ እንዴት መንፈሳውያን መሆን ይቻላል?

በመጽሐፈ መነኮሳት እንደ ተጻፈው በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆነው እንደ ቤተ ክህነት የሚኖሩ፣ በቤተ ክህነትም ሆነው እንደ ቤተ መንግሥት የሚኖሩ ነበሩ፤ አሉ፡፡ ይሁዳ በአካል ከክርስቶስ ጋር ነበር፤ ልቡ ግን ከነ ሊቀ ካህናት ቀያፋ ጋር ጌታን ለመስቀል ያድማል፤ ማርያም እንተ እፍረት በአካል ከአመንዝሮች ጋር ነበረች፤ ልቧ ግን ክርስቶስን ይፈልግ ነበርና ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፡፡ ይሁዳም ልቡ ወዳለበት ሄደ፤ ማርያምም ልቧ ወደ ነበረበት መጣች፡፡ ለመሆኑ ከሁለቱ ሰዎች መንፈሳዊው ማን ነበር?

በአንድ ወቅት አንድ አባት የተናገሩትን እዚህ ላይ ማንሣት ያስፈልጋል፡፡ ለስብሰባ ወደ አንድ መንግሥታዊ ድርጅት ሄጀ ከባለሥልጣናት ጋር ተሰብስቤ ነበር፡፡ በስብሰባው መካከል አንደኛው ባለ ሥልጣን በግእዝ ሲጠቅስ ሰማሁት፤ ተገረምኩ፡፡ ስብሰባው ሲያበቃ ጠብቄ ያንን ሰው «አንተ የቤተ ክህነት ሰው ነህ እንዴ? ቅድም አንድ ነገር ስትናገር ሰምቼሃለሁ» አልኩት፡፡ ሰውዬውም «አዎ ነኝ፤ ምነው ገረመዎት እንዴ» አለኝ፡፡ «የቤተ ክህነት ሰው እንዲህ ባለ ሥፍራ ይኖራል ብዬ አልገምትም ነበር?» ብዬ መለስኩለት፡፡ እርሱም «አባቴ የቤተ ክህነት ሰውኮ በየቦታው አለ፡፡ የቤተ ክህነት ሰው የሌለው ቤተ ክህነት ውስጥ ብቻ ነው» አለኝ ብለው ነገሩን፡፡

## 2 ሙስና

የደብር አስተዳዳሪነት፣ የቤተ ክህነት ሠራተኛነት፣ የውጭ ሀገር ትምህርት እና ሥራ፣ ያለ ገንዘብ የማይገኙበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ትምህርት፣ ችሎታ፣ መንፈሳዊነት እና ሥነ ምግባር መመዘኛ መሆና ቸው እየቀረ ምን ያህል ትከፍላለህ? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ በቤተ ክህነቱ ቦታ ለማግኘት ዋናው መመዘኛ እየሆነ ነው፡፡

ዛሬ ዛሬ በቤተ ክህነቱ ውስጥ ሲሞናዊነት እየተስፋፋ ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በገንዘብ ለመግዛት በሞከረው በሲሞን መሠርይ ስም የተሰየ መው ሲሞናዊነት ሥልጣነ ክህነትን በገንዘብ መግዛት ማለት ነው፡፡

ሲሞናዊነት ቤተ ክህነት ከፍተኛ የሆነ የሙስና ዝቅጠት ውስጥ ሲገባ የሚከሰት ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክህነቷ ኪሳራ ውስጥ በነበረባቸው ዘመናት ሁሉ ሲሞናዊነት ይከሰት እንደነበር ታሪኳ ያሳያል፡፡

ቅስና እና ዲቁና ብቻ ሳይሆን ትልቁ መዓርግ ጵጵስናም ቢሆን የሚገኘው በሲሞናዊ መንገድ መሆኑን ምእመናንም ሆኑ ለቤተ ክህነቱ ቅርብ የሆኑ አካላት ሁሉ የሚያወሩት ጉዳይ እየሆነ ነው፡፡

ጉዳዮችን በገንዘብ እና በገንዘብ ብቻ ለመጨረስ መነሣት፣ ሕንፃዎችን እና ቤቶችን በሙስናዊ መንገድ ማስተላለፍ እየተለመደ ብቻ ሳይሆን ነውርነቱ እየቀረ መጥቷል፡፡ «ዓይነ ኲሉ ሰብእ ይሴፎ ኪያከ**ሚ** የተባለው ለእግዚአብሔር መሆኑ ቀርቶ ለሙዳየ ምጽዋ ቶች እየሆነ ነው፡፡

ለአምሳ እና መቶ አጥቢያዎች ሲተርፉ በነበሩ በአንዳንድ ታላላቅ አድባራት ገንዘብ አልቋል እየተባለ ደመወዝ ለመክፈል ሲቸገሩ ማየታችን ሙስናው ሥጋ ከሙብላት አልፎ አጥንት እስከ መቆርጠም መድረሱን ያመለክታል፡፡ ቤተ ክህነት ቀደምት አባቶች ለችግር ጊዜ መጠባበቂያ እያሉ ያስቀመጡትን ገንዘብ ጨርሶ የየዕለቱን ሙብላት ከጀመረ ሰነበተ፡፡ ለምን?

መንግሥት ሙስና የሥርዓቱ አንዱ አደጋ ነው ብሎ በመለየት ራሱን የቻለ ፀረ ሙስና ተቋም መሥርቶ የዐቅሙን እያደረገ ባለበት ዘመን ቤተ ክህነቱ ሙስናን ለመዋጋት ምንም ጥረት አለማድረጉን፣ ሥርዓት እና አሠራር አለመዘርጋቱን ስናይ ሙስና የሚጠላ ሳይሆን የሚፈለግ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ሙስና በቤተ ክህነቱ መስፋፋቱ ከሌሎቹ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ጋር እየተደጋገፈ ቤተ ክርስቲያኒቱን እየደቆሳት ነው፡

## 3 መንደርተኛነት

አንዳንዶቻችንን በቤተ ክህነቱ ዘረኛነት ያለ ይመስለን ይሆናል፡፡ የቤተ ክህነቱ ዋነኛ ችግር ዘረኛነት አይደለም፡፡ ትግሬ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ኦሮሞ በመሆን የመሳሳብ እና የመጠቃቀሙ ሂደት እጅግ አነስተኛ እና ቢኖርም ለአደጋ የሚያጋልጥ አይደለም፡፡ ዋነኛው ችግር ከዘር ጉዳይ እጅግ የወረደ እና መንደርተኛነት ላይ ያተኮረ ችግር ነው፡፡

በአብዛኞቹ አህጉረ ስብከቶች የሚገኙትን የቤተ ክህነቱን ሠራተኞች ዘር ብንቆጥር በሊቀ ጳጳሱ ዙርያ የሚሽከረከር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ያውም ከአንዲት መንደር ሳይወጣ፡፡ የዋናው ቤተ ክህነትም አሠራር ተመሳሳይ ነው፡፡ በቤተ ክህነት ሀገርህ የት ነው? ማለት  ክልልን፣ ዞንን ወይንም ዘርን አያመለክትም፡፡ ትርጉሙ የተወለድከው የት መንደር ነው? ማለት ነው፡፡

«እምከመ ተለዓልኩ እምድር እስሕብ ኲሎ ሀቤየ» የሚለው የጌታችን ቃል ለመንግሥተ ሰማያት መሆኑ ቀርቶ ለባለ ሥልጣናት የሚተረጎመው በቤተ ክህነት ነው፡፡ አንድ ሰው ባለ ሥልጣን ሆነ ማለት መንደሩ በሙሉ ተጠቃሚ ሆነ ማለት ነው፡፡ ከቻለ ራሱ ይቀጥራል ካልቻለም መባ ሰጥቶ ያስቀጥራል፡፡

መንደርተኛ አሠራር ብቃት ካላቸው ሰዎች ይልቅ ዘመድ ያላቸው ሰዎች በቤተ ክህነቱ ቦታ እንዲይዙ ከማድረጉ በላይ ከላይ ወደ ታች የሚዘረጋ የሙስና መሥመር ለመዘርጋትም ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ በቅጥር መዝገብ ቤተ ክህነቱ የማያውቃቸው ነገር ግን በዝምድናቸው ምክንያት

የቤተ ክህነቱን ጉዳይ በጉቦ የሚያስፈጽሙ አካላት ከቤተ ክህነቱ ውጭ እንዲርመሰመሱ ያደረገውም ይኼ የመንደርተኛነት አስተሳሰብ ከሙስና ጋር በፈጠረው ጋብቻ ምክንያት ነው፡፡

## 4 ኋላ ቀርነት

ሙስና እና መንደርተኛነት እንዲያብቡ፣ ተንሰራፍተውም እንዲቀመጡ ሠላሳ፣ ስድሳም እንዲያፈሩ ያደረጋቸው ደግሞ በቤተ ክህነቱ ዘመኑን የማይመጥን፣ በየትኛውም የዓለም ደረጃ እዚህ ቦታ ነው የማይባል ኋላ ቀር አሠራር መኖሩ ነው፡፡

ይህ ነው የሚባል የፋይናንስ ሥርዓት፣ የሠራተኛ አስተዳደር ሥርዓት፣ የሥነ ምግባር ኮድ፣ የንብረት አስተዳደር ሥርዓት፣ የስብሰባ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት፣ የውሳኔ ማወጃ ሥርዓት፣ የውሳኔ ማስፈጸሚያ ሥርዓት፣ ግልጽ የሆነ የሥልጣን እና ኃላፊነት ደንብ፣ በሌለበት ቤት ሙስና እና መንደርተኛነት ተመችቷቸው ነው የሚኖሩት፡፡

የሙዳየ ምጽዋት አሰባሰብ፣ አቆጣጠር፣ አመዘጋገብ እና ገቢ አደራረግ ወጥ እና ግልጽ የሆነ ሕግ እና አሠራር የላትም፡፡ ይህንን ሥርዓት ለሚያፈርስ የተወሰነ የቅጣት ደንብም የለም፡፡ ከማዘዋወር ያለፈ፡፡ በዚህም ምክንያት ዓይኖቻቸውን በሙዳየ ምጽዋት ላይ አድርገው የሚኖሩ አያሌ ጥገኞችን አፍርተንበታል፡፡

ለአንድ የሥራ መደብ ስንት የሰው ኃይል ያስፈልጋል? በቤተ ክህነቱ ይህ ጥያቄ መልስ የለውም፡፡ ለመሆኑ ለሥላሴ ካቴድራል ስንት ካህናት ይበቃሉ? የሚያውቀው የለም፡፡ በየቀኑ አዳዲስ ሰው ከመጨመር በቀር፡፡ በአንድ ደብር ልክ የሌላቸው ሰባክያነ ወንጌል ከመመደባቸው የተነሣ እስከ አራት የሚደርሱ ምክትል ሰባክያነ ወንጌል እየታዩ ነው፡፡ አራቱም ግን ተመሳሳይ ሥራ ነው የሚሠሩት፡፡

ለመሆኑ የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ለመሆን መመዘኛው ምንድን ነው? መንፈሳዊ መመዘኛው እና ዓለማዊ የዕውቀት መመዘኛው የታወቃል? ፈጽሞ፡፡ በሊቀ ጳጳሱ መልካም ፈቃድ ብቻ ነው፡፡ እስኪ የቤተ ክህነቱ የፋይናንስ ሥርዓት ይታይ፡፡ በመቶ ሚሊዮኖች የሚያንቀሳቅስ ተቋም የታወቀ፣ የተጠና እና ዓለም ዐቀፍ ተቀባይነት ያለው የፋይናንስ ደንብ ለምን የለውም? ለምንስ በውጭ ኦዲተር ኦዲት አይደረግም? ከተደረገስ በይፋ ለምን አይነገርም? ለምንስ በዕቅድ አይመራም? መንግሥት የ2004 በጀቱን በይፋ ተናግሯል፡፡ ለመሆኑ የ2004 የቤተ ክህነቱ በጀት ስንት ነው? የሚያውቀው አለ?

አሁን ያለው የቤተ ክህነት መዋቅር የተዘጋጀው ከሃምሳ ዓመታት በፊት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የተጠና ማሻሻያ አልተደረገለትም፡፡ በዚህም ምክንያት አንዳንድ መምሪያዎች ከኃላ ፊው በቀር ሌላ የሰው ኃይል የላቸውም፡፡ አንዳንድ መምሪያዎችም የሚሠሩት የዕለት ተዕለት ሥራ የላቸውም፡፡ የየመምሪያው ኃላፊዎች በዚያ መምሪያ የተሰየሙበት የሞያ እና የብቃት አግባብነትም የላቸውም፤ ከመመደባቸው በቀር፡፡

ይህ ኋላ ቀር የሆነው አሠራር ለሙስና እና ለመንደርተኛነት አሠራር በሩን ወለል አድርጎ ከፍቶላቸዋል፡፡ ቤተ ክህነቱም ብቃት ያለው አሠራር እና ሠራተኛ እንዳያገኝም በድሎታል፡፡

ዛሬ ሰባኪ የሆነው እና ያልሆነው እንዳይለይ ያደረጉት ኋላ ቀር አሠራር፣ ሙስና እና መንደርተኛነት ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱን እናድሳለን ብለው ለተነሡ አካላት ምቹ የሆነላቸው ቤተ ክህነቱ በኋላ ቀር አሠራር የተተበተበ፣ በሙስና የሚሠራ እና በመንደርተኛነት የታጠረ መሆኑ ነው፡፡ ገዳማት አድባራቱን ለመርዳትኮ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ችግር የለባትም፡፡ ልዩ ጽሕቤቱ በዓመት 40 ሚሊዮን ብር ማውጣት ከቻለ የገንዘብ ችግር የለም ማለት ነው፡፡ የጻድቃኔ ማርያም፣ የቁልቢ ገብርኤልን እና የቤቶች ኪራይን ገንዘብ በሚገባ መጠቀም ከተቻለ ችግር ደኀና ሰንበት ማለት ይቻል ነበር፡፡ ቤተ ክርስ ቲያኒቱ የአሠራር እንጂ የሀብት ችግር የለባትም፡፡

እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ቀድመን ከፈታን ሌሎቹን ችግሮች ሁሉ ሳንፈታቸው ራሳቸው በራሳቸው ይፈቱ ነበር፡፡

ይህንን ሁሉ ችግር ተመልክቶ ቆራጥ መፍትሔ መስጠት የነበረበት ሲኖዶሱ ነበር፡፡ ሕግ ማውጣት፣ አሠራር መዘርጋት፣ ብቁ ባለሞያዎችን መመደብ፣ ችግሮችንም በጊዜ መፍታት የነበረበት ሲኖዶሱ ነበር፡፡ ነገር ግን እርሱ ራሱ ከላይ በተጠቀሱት ሦስት ችግሮች ተተብትቦ ነው ያለው፡፡

እናም ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቅንዓት ያላቸው አባቶች፣ ምእመናን፣ መንግሥት እና የቤተ ክርስቲያኒቱ ወዳጆች ሁሉ አሁን ፊታቸውን የሲኖዶሱን ችግር ወደ መፍታት ማዞር አለባቸው ባይ ነኝ፡፡ የሲኖዶሱ ችግር ሲፈታ የቤተ ክህነቱም ችግር ይፈታል፡፡ የችግሮቹ የስበት ማዕከል እርሱ ነውና፡፡

ቅዱስ ፓትርያርኩም ሆኑ ሌሎቹ የሲኖዶሱ አባላት አሁን ለሚታየው የቤተ ክህነቱ ችግር ዋነኞቹ ተጠያቂዎች እና የችግሮቹም ምንጮች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እንደ እኔ እምነት አሁን ያሉት የሲኖዶስ አባላት እና የሲኖዶሱም አደረጃጀት እነዚህን ሦስት መሠረታዊ የቤተ ክህነቱን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችል ዝግጁነት፣ አደረጃጀት እና ብቃት ላይ አይደሉም፡፡

## ተግዳሮቶቹ

**ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ዘመን አራት ዓይነት ዋነኛ ተግዳሮቶች ገጥመዋታል፡፡**

### 1 የቋንቋ

በሀገር ውስጥ ክልሎች በተለያየ የሥራ ቋንቋ መጠቀማቸውና ትውልዱም በየአካባው ቋንቋዎች ተምሮ ማደጉ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ተግዳሮት ሆኗል። በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚያስተምሩ፣ የሚቀድሱ እና የሚያገለግሉ አገልጋዮችን የማፍራት፣ መጻሕፍይን የመተርጎም፣ አሠራርዋን ከእነዚህ አንፃር የመቃኘት ሥራ አሉባት። በሌላ በኩል ደግሞ ከሀገር ውጭ እየመጣ ያለው ትውልድ የየሀገሩን ቋንቋ ብቻ የሚናገር እየሆነ ነው። ይህንን ትውልድ የቤተ ክርስቲያን ትውልድ አድርጎ መቀጠል ከተፈለገ ለርሱ የሚሆኑ አገልጋዮችን ማፍራት፣ የመማርያ ሥርዓቶችን መቅረጽ፣ አገልግሎቱን ከቋንቋ አንፃር መቃኘት ያስፈልጋል።

## 2 የፖለቲካ

የሀገሪቱም ሆነ የዓለም የፖለቲካ ምሕዳር ተቀይሯል። የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች በአንድ ሀገር የሚፈጠሩበት ሁኔታ ተከስቷል። የአንዲቷ ቤተ ክርስቲያን ልጆች የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች አሏቸው። ለእነዚህ ሁኔታዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ምላሽ ምንድን ነው? ቤተ ክርስቲያን ከተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ጋር ያላት ግንኙነት ምን ዓይነት መሆን አለበት? የድጋፍ? የተቃውሞ? የገለልተኛነት? የዘመኑ ጥያቄዎች ናቸው።

## 3 የማኅበራዊ አስተሳሰቦች

የቤተሰብ፣ የልጆች አስተዳደግ፣ የሥራ፣ የጾታ፣ የሕክምና፣ የአወላለድ፣ ወዘተ ሁኔታዎች እየተቀየሩ አዳዲስ ጥያቄዎችም እየተፈጠሩ ነው። የቤተሰብ ምጣኔ ይፈቀዳል? የትኛው ዓይነት የቤተሰብ ምጣኔ? ማኅፀን መከራየትም ሆነ ማከራየት ይፈቀዳል? ደም መለገስ ይፈቀዳል? የሰውን አካል ማዘዋወር ይፈቀዳል? ጾታ መቀየር ይቻላል? እነዚህን እና ሌሎችን ዘመኑ የፈጠራቸውን ጥያቄዎች በሚገባ መመለስ ገና ይቀረናል።

## 4 የሚዲያ

የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በመላው ዓለም ከመሠማራታቸው እና በልዩ ልዩ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ከመኖራቸው አንፃር ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮዋን ለመወጣት ምን ዓይነት ሚዲያዎች ያስፈልጓታል? እንዴት? የሚሉት ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው። ብዙ ወላጆች ለልጆቻቸው የመማርያ መጽሐፍ፣ ሲዲ እና ዲቪዲ ይፈልጋሉ። ትውልዱ ዲጂታል ትውልድ ሆኗል። ዘመኑ የኢንተርኔት ዘመን ነው። እነዚህን ሚዲያዎች በምን ዓይነት ሁኔታ ብንጠቀምባቸው ጉዳታቸውን ቀንሰን ጥቅማቸውን ልንጨምር እንችላለን?

ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ተግዳሮቶች መመርመር፣ መለየት እና ወቅታዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባታል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የቤተ ክህነቱ መስተካከል፣መጠናከር እና ነጥሮ መውጣት ወሳኝ ነው።

## ፈተናዎች

በአሁኑ ዘመን የሚታተት የኢትዮያ ቤተ ክርስቲያን ፈተናዎች ሦስት ናቸው። የአክራ እስልምና፣ የፕሮቴስታንታዊ ጅሐድ እና የተሐድሶ። ሦስቱም በየዘመናቱ የሚያደርሱት ጥፋት ይለያያል። ዓላማቸው ግን አንድ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱን መለወጥ። ቤተ ክርሰቲያኒቱን መለወጥ ማለትም ዓላማዋን ስታ በሌላ ሐዲድ ላይ እንድትጓዝ ማድረግ ማለት ነው። ዶግማዋን፣ ቀኖናዋን፣ ትውፊቷን እና ቅርሷን በማጥፋት፣ በመበረዝ እና በመቀሰጥ ኦርቶዶክሳዊ ማንነቷን በሌላ ማንነት መተካት ነው።

ሦስቱን ኃይሎች በማጥፋት ቢስማሙም ግባቸው ግን የተለያየ ነው። አክራሪ እስላሞች ማንኛውንም የተለየ እምነት ለማየት ካለመፈለግ የሚመነጭ ነው። ፕሮቴስታንቶች ቤተ ክርስቲያኒቱን ፕሮቴስታንት ማድረግ ነው ዓላማቸው። ተሐድሶዎች ደግሞ የፕሮቴስታንት አስተምህሮ ያላት ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትባል ተቋም መመሥረት ነው።

ስለ አክራሪ ሙስሊሞች እና ስለ ፕሮቴስታንታዊ ጅሐዲስቶች ከዚህ ቀደም አንሥተናል። በነገራችን ላይ አንድ ነገር መጠንቀቅ አለብን። ሙስሊም ሁሉ ወይንም ፕሮቴስታንት የሆነ ሁሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ ጠላት ነው ብሎ ከመፈረጅ። አንድ ሰው ከኛ የተለየ እምነት ስለያዘ ብቻ ጠላታችን አይሆንም። ከኛ የተለየ አስተምህሮ ስላለው ወይንም እኛን ስለሚቃወም ብቻ ከአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ጎራ መፈረጅ የለበትም።

የራሱን እምነት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ በአንድም በሌላም መንገድ መጫን አለብኝ። ቤተ ክርስቲያኒቱም ይህንን ማድረግ ግዴታዋ ነው፤ ያለበለዚያ አስፈላጊውን የጥፋት እርምጃ ሁሉ እወስዳለሁ ብሎ የተነሣው ነው ፀረ ቤተ ክርስቲያን የሚባለው።

ለተሐድሶ ዘመቻ ምቹ ሁኔታ የፈጠሩለት ምንድን ናቸው?

### 1. የቤተ ክህነቱ መዳከም

ካህናትን፣ዲያቆናትን፣መነኮሳትን እና ባሕታውያንን፣ ሰባክያንን እና ዘማርያንን መመዝገብ፣ ዕውቅና መስጠት፣ ማሠማራት እና መቆጣጠር የነበረበት ቤተ ክህነቱ ነበር። ነገር ግን ይህንን የሚያደርግበት የመረጃ ቋት፣ ዶክመንቴሽን፣ አስተዳደር እና ሥርዓት ስለሌለው ማን ካህን፣ማን ዲያቆን፣ ማን መነኩሴ፣ ማን ባሕታዊ እንደ ሆነ፣ ማን ሊያስተምር ማንስ ሊዘምር እነደተፈቀደለት እና እንደሚችል የሚታወቅ ነገር የለም።

በዚህ የተነሣ ባሕታዊ ነበርን ተለወጥን፣ መነኮሳት ነበርን ተለወጥን እያሉ መመስከር እየተለመደ መጥቷል። ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚሳደቡ መጻሕፍት እና መጽሔቶች የሚወጡት በመሪጌቶች እና በዲያቆናት ስም ነው። በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተቋማት ተሐድሶዎቹ በግልጽ ሲንቀሳቀሱ ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ ስሕተታቸውን ለመሸፋፈን ጥረት የሚደረገው በቤተ ክህነቱ ነው።

አንዳንዶቹም ቤተ ክርስቲያኒቱን የማጥፋት ሥራቸውን የሚሠሩት የቤተ ክህነቱን ሥልጣን ተገን አድርገው ነው።

## 2. የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን ድጋፍ

በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች የተሐድሶን እንቅ ስቃሴ በሥልጠና፣ በፋይናንስ እና በዲፕሎማሲ ይደግፋሉ። ከውጭ ሀገር ድረስ መጥተው በተሐድሶ የማሠልጠኛ ጣቢያዎች ሥልጠና የሚሰጡ አሉ። ፕሮጀክቶ ችንም በገንዘብ ይደግፋሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ ርምጃ መውሰድ ስትጀምር ደግሞ የመ ብት ረጋጣ ተካሄደ እያሉ በየሚዲያው ይለፍፋሉ።

## 3. የሚገባቸው አካላት አለመሥራት

ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ ከሰዋስወ ብርሃን ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ የአብነት ትምህርት ቤቶች የሚወጡ ደቀ መዛሙርት ከመድረኩ ርቀው የቢሮ ሥራ ላይ ተጠምደዋል። ዛሬ ደግሞ ሕዝቡ የሚሰማው የሚ ናገረውን፣ የሚጽፈውን እና የሚዘምረውን ነው። በ1980ዎቹ እና 90ዎቹ በስብከተ ወንጌሉ አገልግሎት ላይ በስፋት እና በትጋት ተሠማርተው የነበሩት እንደ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ጽርሐ ጽዮን የአንድነት ኑሮ ማኅበር የመሳሰሉትም በሌሎች አገልግሎቶች ተይዘው መድረኩን እየተውት መጥተዋል።

ይህ ደግሞ ለሌሎች ጆቢራዎች እና ጥቅምን ከተሐድሶ ንቅናቄ ጋር አያይዘው ለሚሠሩ አካላት በር ከፈተላቸው:: በር መክፈት ብቻም ሳይሆን አገሩን አስረከባቸው::

## 4. ከዶግማዊ ወንጌል ወደ ማኅበራዊ ወንጌል መሸጋገር

የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት፣ ቅዳሴያት፣ ጸሎቶች እና ሥርዓቶች የሚያሳዩን አንድ ነገር አለ። የቤተ ክርስቲያኒቱ የአገልግሎት ማዕከል ነገረ ድኅነት መሆኑን:: ነገረ ድኅነት ደግሞ ከቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት ትምህርት ጋር ፈጽሞ የተያያዘ ነው:: በመሆኑም የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በነገረ መለኮታዊ ትምህርት ይታወቃሉ::

በአሁኑ ዘመን ግን የፕሮቴስታንቱን ዓለም ወደ ሴኩላሪዝም የወሰደው ማኅበራ ወንጌል በቤተ ክርስቲያናችን በስፋት እየሠረገ ይገኛል። ትምህርቶቻችን ድኅነት ተኮር መሆናቸው ቀርቶ ድህነት ተኮር ሆነዋል። ከድህነት መውጣት፣ ሥራ መያዝ፣ ዲቪ ማግኘት፣ ውጭ መሄድ፣ ከበሽታ መዳን፣ ባለ ቤት እና ባለ መኪና መሆን፣ ማስደሰት እና ማዝናናት የስብከቶቻችንም የመዝሙሮቻችንም ማዕከል ሆኗል::

አብዛኞቹ መዝሙሮቻችን እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ፣ ሥራውን የሚገልጡ፣ የመ ዳናችንን መንገድ የሚያመለክቱ እና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የያዙ ሳይሆኑ ከድህነት የመውጫ መንገድን የሚያሳዩ ናቸው:: ገደል፣ ጫካ፣ ተራራ፣ ሸለቆ፣ ጨለማ፣ የበዛባቸው ናቸው:: ክሊፖቻቸውም እግዚአብሔር ድንቅ አደረገልኝ ብለው ቪላ ቤት፣ ለዚህ አደረሰኝ ብለው ቶዮታ መኪና፣ ሰው አደረገኝ ብለው ላፕ ቶፕ፣ በከፍታ ላይ አስኬደኝ ብለወ አውሮፕላን የሚያሳዩ ሆነዋል::

ይሄ ሁኔታ ሕዝቡ ሃይማኖቱን ከማወቅ ይልቅ ችግሩን ብቻ እህህ እንዲል፣ የስብከት ዓላማው መዳን መሆኑ ቀርቶ ማኅበራዊ ርካታ ማግኘት እንዲሆን አደረገው:: የተሐድሶ ንቅናቄ ሲመጣ ሕዝቡ ክፉውን ከደግ መለየት ያቃተው የሁሉም ድምጽ አንድ ሆኖበት ነው::

## 5. አገልግሎት ሥራ መሆኑ

አገልግሎቱ በማይገባቸው እጅ ሲገባ አገልግሎት መሆኑ ቀረና ሥራ ሆነ። ስብከት ሥራ ነው:: ዘማሪነት ሥራ ነው:: ፕሮግራም መምራት ሥራ ነው:: አንድ የገጠር ጉባኤ ለመሄድ በትንሹ አምስት ሺ ብር ክፍያ ይጠየቃል። እንዲያውም አንዳንዴ ሙሉ ነው፣ ግማሽ፣ ሩብ፣ እየተባለም ምርጫ ይቀርባል:: ሙሉ ማለት ሰባኪ፣

ሁለት ሦስት ዘማሪ፣ ፕሮግራም መሪ፣ የክራር ተጫዋች፣ የመሰንቆ መች፣ ሞንታርቮ፣ አንድ ላይ ማለት ነው:: ይኼ ሲሆን ክፍያው እስከ አርባ ሃምሳ ሺ ብር ይደርሳል::

ግማሽ ማለት አንድ ሰባኪ አንድ ዘማሪ፣ እና አንድ የመሣርያ ተጫዋች ማለት ነው ክፍያው ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ይሆናል:: ሩብ ማለት ደግሞ ሰባኪው እና ዘማሪው ብቻ ሲሄዱ ነው:: ይህኛው ይረክሳል:: እስከ አሥር ሺ ብር ይገኛል::

አንድ የስብከት ካሴት ማስተሩ እስከ አንድ መቶ ሺ ብር በሚያወጣበት፣ አንድ የመዝሙር ማስተር እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር በሚሸጥበት ዘመን ላይ ነን:: ጉባኤ እናዘጋጅና በፐርሰንት እንካፈል መባል ነውር መሆኑ ቀርቷል:: ገበያው በመድራቱ የተነሣ በአሁኑ ጊዜ ከሦስት መቶ በላይ የመዝሙር ካሴቶች በዓመት ይወጣሉ:: ስብከት እና መዝሙርም ክፍት የሥራ ቦታ ሆኗል::

ከጨዋ ዘማርያን እና ሰባክያን በስተቀር ሌሎቹ ስብከት እና ዝማሬ እንጀራቸው ነው:: መናገር እና ድምጽ እንጂ ዕውቀት እና እምነት ለአገልግሎት አይጠየቁም::

ተሐድሶዎች ይህንን የተበላሸ መሥመር ነው በሚገባ የተጠቀሙበት:: ዛሬ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲነገር ስለ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት እና ሊቃውንት ሳይሆን ስለ ጥቂት ዲያቆናት እንዲነገር ያደረገውም ይኼው መሥመር ነው::

## 6. ቤተ ክርስቲያኒቱ ያልጨረሰቻቸው ጉዳዮች መኖር

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አያሌ የመከራ ወቅቶችን አልፋ እዚህ የደረሰች ጽንዕት ቤተ ክርስቲያን ናት:: በመከራዎቿ ብዛት ምክንያት ያልጨረሰቻቸው ሥራዎች አሏት:: መጻሕፍቷን ሠፍራ እና ቆጥራ አልጨረሰችም:: መልስ ቢኖራቸውም መል ሷን ያልገለጠችባቸው ጉዳዮች አሉ:: በቤተ ክርስቲያን ስም የሚወጡ ነገሮች የቤተ ክርስቲያኒቱን ቡራኬ እና ፈቃድ የሚያገኙበት ሥርዓት የለም::

አገልጋዮቿ በቁርጥ አይታወቁም:: ስሟን ለሚያጠፉት ሰዎች ይህ እኔን አይመ ለከትም የምትልበት መንገድ አልፈጠረችም:: አንዳንድ ጊዜ በህብትነት በያዘቻቸው ነገር ግን የርሷን እምነት እና ሥርዓት በማያንጸባርቁ ነገሮች ሁሉ ተጠያቂ ትሆናለች:: የግራኝን ካባ፣ የሕንዶችን የብርሃማኒስት መጽሐፍ፣ የአሪስቶትልን እና የፕላቶን ፍልስፍና ቿብቃ ያቆየች መሆንዋ ተረስቶ ሁሉም የርሷ ጥፋት እየሆነ ይነገርባታል::

ቤተ ክርስቲያን የርስዋ የሆኑትን ሠፍራ እና ቆጥራ በመግለጥ የማይመለከቷትን አይመለከቱኝም ማለት ባለመቻሏ ስሟ በከንቱ እየጠፋ ነው።

በዚህ የተነሣ ዛሬ ተሐድሶ በየገዳማቱ ተሠግስጎ ቅዱሳት መካናትን ለመቀሰጥ እየጣረ ነው። በቤተ ክርስቲያኒቱ የትምህርት ተቋማት ሠርጎ ትምህርቷን ለማስለወጥ እየሠራ ነው። ቤተ ክህነቱን ተገን አድርጎ ተሐድሶን ያነሣ ውሾ እያስባለ ነው። በዓመት ከ67 በላይ ቤተ ክርስቲያንን የሚፃረሩ መጻሕፍት ያሳትማል፣ ሰባት ጋዜጦችን እና አምስት መጽሔቶችን ያዘጋጃል። አራት ዌብሳይቶች ከፍቷል።

## ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ በየዘመናቱ የሚነሡ አጽራረ ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት በእነርሱ ዐቅም መጠን ሳይሆን በእኛ ዝግጅት እና ጥንካሬ መጠን የሚለካ ነው። አርዮስ ቢነሣ አትናቴዎስ ነበረ። ንስጥሮስ ቢነሣ ቄርሎስ ነበረ፤ ልዮን ቢነሣ ዲዮስቆሮስ ነበረ። ካቶሊኮች በ16ኛው ክዘን ቢነሡ እነ እምነ ወለተ ጴጥሮስ፣ እነ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ፣ ነበሩ። ጣልያን አምስት ዓመት መከራ ቢያመጣ እነ አቡነ ጴጥሮስ ተነሥተውላት ነበር።

አጽራረ ቤተ ክርስቲያን እንዳይነሡ ማድረግ አይቻልም። እንክርዳዱን የሚዘራው ሌላ ነውና። መፍትሔው እንክርዳዱ በስንዴው መካከል እንዳይዘራ ነቅቶ መጠበቅ፣ ከተ ዘራም እርሻውን ፈጽሞ ከመዋጡ በፊት በጊዜ ማረም ነው። ጌታችን በማቴ. 13÷21 ባስተማረን የስንዴው እና የእንክርዳዱ ምሳሌ ጠላት እንክርዳዱን የዘራው የስንዴው ቿ ባቂዎች በተኙ ጊዜ ነው።

ምንጊዜም እንክርዳዱን በስንዴው ውስጥ እንዲበቅል፣ በቅሎም ስንዴውን እስከመዋጥ ድረስ እንዲደርስ የሚያደርገው፣ ሲብስም ማረም እስከማይቻልበት ደረጃ የሚያደርሰው የገበሬዎቹ መተኛት ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮች፣ ተግዳሮቶች እና ፈተናዎች ይኖራሉ። ፈተናዎቹ እና ተግዳሮቶቹ ከውጭ ወደ ውስጥ የሚመጡ ናቸው። ችግሮች ግን ከውስጥ ወደ ውጭ የሚመጡ ናቸው። እኛ ውስጣችንን ካጠነከርን የትኛውም ዓይነት ፈተና ቢመጣ አያስ ጨንቀንም። «ነፋስም ነፈሰ፣ ጎርፍም ጎረፈ፣ ያንንም ቤት መታው፣ ግን አላናወጸውም» እንዲል ወንጌል።

እንደ እኔ የአጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ፍላጻ ሊመክት የሚችል መንፈሳዊነት፣ ዝግጁ ነት፣ አሠራር፣ አወቃቀር፣ ኅብረት፣ ትምህርት፣ ዕቅድ፣ ካለ ሌላው ሁሉ ዕዳው ገብስ ነው።

በአባቶች እና በምእመናን መካከል አሁን የሚታየው ክፍተት ካልተሞላ፣ ቤተ ክህነቱ ለዘመኑ በሚመጥን፣ የምእመናኑን ፍላጎት በሚያረካ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልግሎት በሚያቀላጥፍ፣ ችግሮችን በጊዜያቸው በሚፈታ፣ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን በሚመክት መንገድ ካልተዋቀረ መናፍቃን ሳይሆኑ ራሳችንን የምንጎዳው ራሳችን እንሆናለን።

እናም የውስጥ ችግራችንን ለመፍታት እና ለውጪ ፈተና እና ተግዳሮት ዝግጁ ለመሆን ትኩረት እንስጥ።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችንን ይጠብቅ።